## ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የሚደረግ ትግል የግድ የሚለው የትብብር ጥያቄ

ብርሃኑ ነጋ[1]

ግንቦት 2000 አም

### 1. መግቢያ

ከጥቂት ወራት በፊት በሎስ አንጀለስ ከተማ በተደረገ የኢትዮጵያውያን ስብሰባ ላይ ባደረግሁት ንግግር በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማምጣት የሚደረገው ትግል አመርቂ ውጤት እንዲያስገኝ በትግሉ ውስጥ የሚሳተፉ ሀይሎች መመለስ ያለባቸው አስፈላጊ ጥያቄዎች አሉ በሚል በሶስት ክፍል የተከፈሉ ወደ ሰላሳ ግድም የሚሆኑ ጥያቄዎችን መደርደሬ ይታወሳል:: በጊዜውም አድማጮቼን በጥያቄዎቹ ላይ አጥብቀው እንዲያስቡባቸው ብቻ ሳይሆን ቢቻልም በቡድን እንዲወያዩባቸው ከመጋበዝ አልፌ እኔ እራሴ በእነኝህ ጥያቄዎች ላይ በጥንቃቄ አስቤ ለራሴ አጥጋቢ የምለው መልስ እስከማገኝ ድረስ ከህዝብ ጋር የሚደረግ ማንኛውም አይነት ስብሰባ ላይ እንደማልሳተፍ ገልጩ ነበር::

ይህንን ጉዳይ በግሌ እያሰብኩበት እና በብዙ መልኩ በአመለካከት ከምንቀራረብ ወዳጆቼና ከአንዳንድ የቀድሞ የድርጅት አባላት ጋር እየተወያየሁበት እያለ ነበር ከሁለት ሳምንታት በፊት ቀድሞ በቅንጅት ላእላይ ምክር ቤት ያለን አምስት ሰዎች በሰፊው መክረንበት እንደመንግስታቸው በአይን አውጣነት በቅንጅት ስም ከሚንቀሳቀሱትም ሆነ ቀድሞ የቅንጅት አመራር አባላት ከነበሩትና በዚህ ሀፍረተ ቢስ መንግስት ስማቸውን በመቀማታቸው ምክንያት ሌላ ስም አውጥተው በህጋዊነት ለመንቀሳቀስ ከሚሞክሩት የቀድሞ ባልደረቦቻችን መለየታችንን ያስታወቅነው:: ከድርጅቱ ለመለያየታችንም ዋናው ምክንያት ከዚሁ ከትግል ስልት ጋር በተያያዘ ባለን ልዩነት ምክንያት መሆኑን ምንም በማያሻማ ሁኔታ ለሚመለከተው ሁሉ የገለፅነው:: ይህ የመልቀቂያ ደብዳቤያችን እንደወጣ ከተለያየ ቦታ የሰማሁትና በሰፊው የተበተነው አመለካከት በሎስ አንጀለስ ላነሳሁዋቸው ጥያቄዎች ቢያንስ ለራሴ የሚበቃ አመርቂ መልስ ማግኘቴን የሚያመላክት ሆኖ መወሰዱ አልቀረለትም:: ይህ ደግሞ በቶሮንቶ ካደረግሁት ንግግር ጋር ተዳምሮ የመልሴን ምንነት «እቅጩን» እንዳገኙት ሳያስተማምናቸው አልቀረም::

ዛሬ ልናገርበት የመረጥኩት እርእስ ግን በተዘዋዋሪ መንገድ ይነካካው እንደሆነ እንጂ በቀጥታ የትግል ስልትን የሚመለከት አይሆንም:: ይህን ጠብቃችሁ የመጣችሁ ካላችሁ ልባችሁን ስላላረካሁት ከወዲሁ ይቅርታ እጠይቃለሁ:: ይልቁንም ዛሬ ላተኩርበት የፈለግሁት ርእስ በዚሁ በሎስ አንጀለስ ንግግሬ ላይ በሶስተኛ ክፍል ያነሳሁዋቸውን ወደ ሰባት የሚሆኑ ጥያቄዎችን በመጠኑም ለመመለስ እንዲያስችሉ በጣም አስፈላጊ ናቸው በምላቸው በአብዛኛው የሀሳብና

---

[1] ግንቦት 3፤ 2000 ዓ.ም:: ሲአትል ከተማ ለኢትዮጵያውያን የተደረገ ንግግር::

የተግባር ክርክሮች ላይ ነው። የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሁኔታ ፈርዶበት እንደኔ ከልጅነቱ ለተከታተለ ሰው ዛሬ ደፍሬ ልናገርበት ያሰብኩትን የዘውግ ጉዳይን ያክል በከፍተኛ ደረጃ ስሜትን የሚቀሰቅስ፤ በብዙ መልኩ ደግሞ ከምክንያታዊ ክርክር የራቀ፤ በዚያኑ ያክል ደግሞ ለአብሮነታችንና በእርግጥም ለወደፊቱ በእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ስር ለመኖር ካሰብን በሰላማዊና በሀቀኛነት እንዲሁም በጥልቅ አምክህኖታዊ መንገድ መፍታት ያለብን ሌላ ጉዳይ ያለ አይመስለኝም። ጉዳዩ የእያንዳንዳችንን ማንነት የሚነካ ስለሆነም በግልፅ ለመወያየትም እንፈራዋለን። ስለዚህም ፊት ለፊት ከመነጋገርና ለመተማመን ከመሞከር ይልቅ በኮድ እናወራዋለን። በግልፅ አለማውራቱ ደግሞ የአመለካከት ጥራት እንዳይኖረን ይከለክለናል። የአመለካከት ጥራት ከሌለን ደግሞ መፍትሄ ለመስጠት ይቸግረናል። ዛሬ ባለችኝ አቅም ለመሞከር የፈለግሁት የጉዳዩን ለእኛም ሆነ ለልጆቻችን፤ ለእውነተኛ ዴሞክራሲም ሆነ ለዘላቂ ሰላም እጅግ አስፈላጊነት በመገንዘብ በተቻለ መጠን በስሜት ከማይነዳ፤ የአእምሮ ሚዛናዊነትንና የሌላውን ህመም ለመረዳት ከሚፈልግ አዛኝ ልቦና ጋር ሆነን እንድንመለከተው ለመሞከር ነው።

ይህን ስል ጉዳዩ ስሜት መቀስቀስ አይገባውም ከሚል በአየር ላይ ከሚንሳፈፍ የዋህነት በመነሳት አይደለም። ወይንም ደግሞ ስሜታዊነት (emotions) በራሳቸው ምንም ፋይዳ የሌላቸው ለእውቀታችንም ሆነ ለአጠቃላይ ህይወታችን የሚጨምሩት ነገር የለም ከሚል የተጣበበ የፍልስፍና መሰረት በመነሳት አይደለም። እንዲያውም ስሜታዊነት፤እልህና የመሳሰሉት ስሜቶች እንደሁኔታው ተገቢ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊም የሚሆኑበት ጊዜ እንደሚኖር በማመን ነው። በማሰብና በማሰላሰል ለሁሉም የሚጠቅምና ሁሉንም አሸናፊ የሚያደርግ መፍትሔ ሊኖር እየቻለ በስሜት በመነዳት ከመፍትሄው እየራቅን ሁላችንንም ወደማይጠቅም መንገድ እንዳንሄድ ለመከላከል ብቻ ነው።

እኔ እንደታዘብኩት በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ጊዜ ተከራካሪ ወገኖች ስሜታዊ ሆነው የሚናገሩት አእምሮአቸው–እውነት ነው ብሎ ከሚነግራቸው ጋር ይለያያል። ወይም ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ከልባቸው የሚያምኑበት ነገር በተለይ በዘመናችን በማህበረሰቡ ዘንድ በፍፁም ተቀባይነት እንደሌለው ስለሚያውቁ ያንን እምነታቸውን በቀጥታ ለውይይት ከማቅረብ ይልቅ ብዙ ሊያከራክር የማይገባ ትንሽ ጫፍ ይይዙና በሱ ላይ ልብ አውልቅ ክርክር ያደርጋሉ። አንዳንዱ ጭቅጭቅ በአብዛኛው ሁሉም ወገን የሚስማማበትን ነገር በመጀመሪያ በግልፅ ካለማውጣትና በዚህም ብዙ የጋራ መግባባት መኖሩን ካለመረዳት በልዩነቶች ላይ ብቻ በማተኮር የሚደረግ ጉንጭ አልፋ ንትርክ አለ። ሁሉም ግን ልዩነቶችን ለማጥበብና ወደ መግባባት ለማድረስ አይጠቅሙም። በሌላ በኩል ግን ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በእርግጥም ለወደፊቱ የፖለቲካ ህይወታችንና ለሰላማችን አስፈላጊ የሆኑና በደንብ ክርክር የሚደረግባቸውና መፍትሄም

የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች አሉ። የውይይታችን አትኩሮት እዚያ ላይ ሊሆን ይገባል። እኔም በዛሬ ውይይት ላይ የማተኩርባቸው በአብዛኛው እንደነዚህ አይነት ጉዳዮች ላይ ይሆናል። አሁን አገራችን ያለችበት ሁኔታ፣ በነመለስ፣ ስብሀትና በረከት እየተፈፀመ ያለው ግፍና አስነዋሪ ድርጊት አፎቱን ሞልቶ እየፈሰሰ ባለበት ጊዜና፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ለመብታችን በጋራ ታግለን ነፃነታችንን ለመጎናፀፍ እንዳንችል እነኝህ መሰሪ ሰዎች እየተጠቀሙበት ያለው ዋናው ስልት ሁላችንንም በዘውግ (በብሄር) በመከፋፈል ሆን ብሎ ማራራቅ መሆኑን ባወቅንበት ሁኔታ በዚህ ጉዳይ ላይ በጥልቅ ያሰበና ወደ መቀራረብ የሚያመጣ ውይይት ከማድረግ መቆጠብ ከአላዋቂነት አልፎ ፍፁም ጅልነት የሚሆንበት ደረጃ ላይ እየደረሰ ይመስለኛል።

በእኔ እምነት ይህን ውይይት በጥሩ ሁኔታ ካደረግነውና በዚያ ላይ ሰፋ ያለ ማህበራዊ ስምምነት ማዳበር ከቻልን ከትግል ስልትም በበለጠ ለወደፊቱ ህይወታችን ፋይዳ ያለው ነውና የሚሆነው በአፅንኦት ትከታተሉኛላችሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በማነሳቸው ነጥቦች ላይ ልዩነትም ካላችሁ በቀና አስተሳሰብ ውይይት ለመጫሪያ የተሰነዘረ መሆኑን ተረድታችሁ የተሻለውን መንገድ ታሳዩኛላችሁ፣ በዚህም መንፈስ በሚደረግ ውይይት ጤናማ ወደሆነ የጋራ አመለካከት እንሄዳለን፣ በዚህም ሂደት ኦባማ እንደሚለው ሁላችንም ተያይዘን እንነሳለን፣ የምንወዳትን አገራችንን አብረን እናነሳታለን እንጂ እርስ በእርስ ተጉዋትተንና ተሰነጣጥቀን እንጦርጦስ የምንገባበትን ሁኔታ እንደማንፈጥር ተስፋዬ ነው።

በቀጥታ ወደ ውይይቱ ከመግባቴ በፊት ግን የተለመደ ምስጋናዬን ላቅርብ። ወደዚህ አካባቢ እንድመጣ የጋበዙኝ እዚህ በሲአትል የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ፕሮግራሙን ባዘጋጁበት ጊዜ ቫንኩቨርም ቅርብ ነውና፣ያሉትም ኢትዮጵያውያን ቁጥራቸው ትንሽ ነውና፣ እግረ መንገድህን ብትጎበኛቸው ብለው እዚያ ካሉት ኢትዮጵያውያን ጋር በመመካከር ነው የጋበዙኝ። በመጀመሪያ ለትብብራችሁና ለቀና ስሜታችሁ ላመስግን። እኔ የምወረውረው ሀሳብ ምናልባት ይጠቅም ይሆናል ብላችሁ የአዘጋጆቹን ግብዣ አክብራችሁ ለመጣችሁ እድምተኞችም ከፍተኛ ምስጋና ይድረሳችሁ። በተለይም በተለመደው «የኢትዮጵያዊ ጨዋነት» ሰው በተጋበዘበት ሰአት በእቅጩ ከመጣ «የቀላዋጭነት ምልክት» መሆኑን ገምታችሁ ነው መሰል ከተጋበዛችሁበት ጊዜ አንድ ሁለት ሰአት አሳልፋችሁ በመምጣት «እውነተኛኢትዮጵያዊነታችሁን» በማስመስመስከራችሁ የኢትዮጵያ አምላክ ያክብራችሁ እላለሁ። እንደሚታወቀው ትላንት በቫንኩቨርና ዛሬም እዚህ ሲአትል የማደርገው ስብሰባ እኔ ከቅንጅት በኦፊሴል ከወጣሁ የመጀመሪያዬ መሆኑ ነው። በዚህም ምክንያት ትንሽ «ክብሬ» ሳይቀንስ አልቀረም። በቶሮንቶ በነበርኩ ጊዜ ለእኔ ትልቅ ክብር ሰጥተው፣ እኔ የምናገረው ነገር አገር ሊያናውጥ የሚችል አደገኛ ነገር መሆኑን ማለቂያ በሌለው እውቀታቸው ተገንዝበው (ጥቂትም ቢሆኑ) የተሰለፉትን ወገኖቻችንን ካየሁ በሁዋላ ተመሳሳይ ክብር እዚህም ይጠብቀኛል ብዬ ነበር። ይህ ባለመሆኑ የደረሰብኝን ከፍተኛ የሞራል ጉዳት እንድትገነዘቡልኝ በኦፊሴል አስታውቄ ወደ ውይይቱ ልግባ።

አድማጮቼ ውይይቱን ለመከታተል እንዲመቻችሁ የንግግሬን ቅደም ተከተል በቅድሚያ ላስታውቃችሁ:: በመጀመሪያው ክፍል በጋራ መታገል ለምን እንደሚያስፈልግ ብዙዎቻችሁ ልትስማሙበት የምትችሉትን ምክንያቶች አቀርባለሁ:: በመቀጠልም ትንሽ አከራካሪ ወደሆነው በጋራ መታገል እንደዚህ የሚጠቅም ከሆነ ይህንን ለማድረግ እስከአሁን ለምን እንዳልቻልን ያሉኝን መላምቶችና መከራከሪያዎች አቀርባለሁ:: በሶስተኛው ክፍል የጋራ ትግሉ አስፈላጊ መሆኑን በመቀበል በተግባር ወደፊት ለመሄድ እንድንችል የሚያስፈልገው የአስተሳሰብ ለውጥ ላይ ጥቂት እላለሁ:: በመጨረሻው ክፍል የጋራ ትግሉ ጊዜያዊ ሳይሆን ዘላቂ ውጤት እንዲሰጥ በተግባር መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች ያሉኝን አንዳንድ ሀሳቦች አቀርብና ሃሳቤን አጠቃልላለሁ::

## 2. የጋራ ትግል ለምን ያስፈልጋል?

ከላይ ባስቀመጥኩት የውይይት መርሀ ግብር ውስጥ በቀጥታ ከመግባቴ በፊት ግን ውይይቴ መነሻ ያደረጋቸውን አንዳንድ እሳቤዎች ከወዲሁ ላስቀምጥ:: በመጀመሪያ ከላይ እንደጠቀስኩት ዛሬ ለመወያያ የመረጥኩት ርእስ ከዘውግ ጋር የተገናኙ ጥያቄዎች ላይ እንደመሆኑ የጋራ ትግልን በሚመለከት ከዚህ በታች የማቀርበው አስተያየት በተለይ የሚያተኩረው በዘውግ (በብሄር) በተደራጁና ዘውግ ዘለል (ህብረ ብሄር) በተደራጁ ሀይሎች መሀከል ያለውን ነው::[2]

ሁለተኛ ይህ ውይይት በኢትዮጵያ ያሉ የፖለቲካ ሀይሎች በሙሉ በኢትዮጵያውያን መሀከል ፍፁም እኩልነት መኖር እንዳለበትና ምንም አይነት በዘር፤ በሀይማኖት፤ በፆታ፤ በባህል...ወዘተ ላይ የተመሰረተ አድልዎ እንዲኖር አይፈልጉም ብሎ ይነሳል:: ይህ ትንሽ ሊያሳስት የሚችል አቀራረብ ስለሆነ ትንሽ ላብራራው:: ይህን ማለት ግን ሁሉም በውስጣቸው ሰዎች ወይንም ዘውጌ ማህበረሰቦች በርግጥም እኩል ናቸው ብለው ያምናሉ፤ አይንቁም፤ እድሉን ቢያገኙ እንዲህ አይነት አድልዎ ለመፈፀም የሚሹ አስተሳሰባቸው በስብስቴ ጊዜ እንደነበረው የቆመ ሀይሎች የሉም...ወዘተ ማለት አይደለም::[3] ወይንም ደግሞ እንዲህ አይነት አድሎዎች በአሁኑ ጊዜ በፍፁም የሉም ለማለት አይደለም:: ግን አድልዎ ተገቢ ነው፤ እኔ ወይንም እኛ ከሌላው የተለየን ወይንም የተሻልን ነን፤ የበለጠ የመግዛት መብት ያለን እኛ ነን ወይንም ደግሞ በታሪክ ስለተበደልን አሁን የመግዛት መብቱ የኛ ነው ብለው አፍ አውጥተው የሚናገሩ ከምር ሊወሰዱ

---

[2] እዚህ ላይ የጋራ ትግል ለማድረግ ችግር የገጠመው በሁለቱ አይነት ሀይሎች ብቻ ሳይሆን በያንዳንዳቸው መሀልም መሆኑ ጠፍቶኝ አይደለም:: ይህ የሆነበት ምክንያት የተለያየ መሆኑን ከማመንና ሁሉንም ጉዳዮች በዚህ ፅሁፍ ላይ ከመዳሰስ ይልቅ በዚህኛው ምክንያት ላይ የበለጠ ለማነጣጠር ከመፈለግ ነው::

[3] እዚህ ውይይት ላይ ሰዎች በዘልማድ፤ ባለመጠንቀቅ፤ ወይንም ደግሞ በሰዎች መሀከል ያሉ ልዩነቶች ላይ በተመሰረቱ የተጠቂውን ስሜት ለመጉዳት ሳይሆን ለቀልድ በሚል የሚጠቀሙባቸውን ንግግሮችና አስተያየቶች፤ በተጎጂ ሰዎች ስሜት ላይ ሊፈጥር የሚችለውን የስነልቡና ጠባሳ፤ ይህም የሚፈጥረውን የማራራቅ ስሜት በውይይቱ ውስጥ የችግራችን አካል አድርጌ አልወሰድኩዋቸውም:: እነኝህ ከሞላ ጎደል በሁሉም አገሮችና ህዝቦች መሀከል የሚታዩ፤ በተገቢው ስልት ከተያዙ መሰረታዊ ችግር ሊፈጥሩ የሚችሉ ሊሆኑ አይገባቸውም ከሚልና በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ብቻ እንዲያተኩር በሚል አላተኮርኩበትም::

የሚችሉ የፖለቲካ ሀይሎች የሉም ለማለት ነው። ይህም ስለሆነ ነው እንዲህ አይነት ስሜቶች እንዳሉ እየታወቀም፤ አንዳንድ ጊዜም እንዲህ አይነት እምነቶችና ልዩነቶች ሆን ተብሎ ለፖለቲካ ጥቅም እየዋሉም፤አድራጊዎቹ በስውር የሚያደርጉት። ችግሩንም በጊዜ ለማስወገድ የሚቸግረውም ለዚህ ነው።

ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያ የተለየ ነገር አይደለም። በአሜሪካ ፖለቲካ ዘረኛነት በተዘዋዋሪነትና በስውር በተግባር እየዋለም (ለምሳሌ አሁን በሚካሄደው ምርጫ) ማንም ፖለቲከኛ በግልፅ ዘረኛ ነትን የሚያንፀባርቅ ነገር ሊናገር ወይንም በአድልዎ አምናለሁ ብሎ ከምር ሊወሰድ አይቻለውም። እንዲህ አይነት ግልፅ የመድሎ አመለካከት ከፖለቲካ ቁዋንቁዋው መውጣቱ ደግሞ በሁለት ወገን ጥቅም አለው። በአንድ በኩል ያ የፖለቲካ ማህበረሰብ ግልፅ አድልዎን አለመቀበሉና (ወይንም የፖለቲካ ትርፍ እንዳያስገኝ ማድረጉ) አንዳንዴም አድሎ አፀያፊ መሆኑን ማህበረሰቡ መገንዘቡ ቀስ እያለ የሚፈጥረው አወንታዊ የሆነ (በተለይ በወጣቶችና በህፃናት አካበቢ እያደር የሚበለፅግ) የባህል ለውጥ አለ። ሁለተኛ አድሎን በኦፊሴል የሚቀበል የፖለቲካ ሀይል የለም ማለት አድሎን ህጋዊ መሰረት ለመስጠት ያስቸግራል ማለት ነው። ስለዚህም በደንብ የሚሰራ የሕግ ተቁዋም ባለበት ቦታና የፖለቲካው ስርአት የሕግ የበላይነትን በተቀበለበት ሁኔታ በአጭር ጊዜ የአድሎን ሁለንተናዊ መሰረት በመናድ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ጤናማ ማህበረሰብ ለመፍጠር ይቻላል። ለዚህ ውይይታችን ይህንን እሳቤ መውሰዱ ከዚህ እይታ ውጪ ያሉትን የፖለቲካ ሀይሎች እውነተኛ አክራሪነት ማህበረሰቡ ተገንዝቦ የፖለቲካ ጊዜውን ከእነሱ ጋር በመንገታገት እንዳያጠፋው ያደርጋል። ይልቁንም ውይይቱ ትርፋማ በሆነውና የሰዎችን እኩልነት ከልባቸው በተቀበሉ ያም ሆኖ ግን በተለያየ ምክንያት በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ እውነተኛ ልዩነቶች ላይ እንዲያተኩሩ፤ ብሎም በሰጥቶ መቀበል የድርድር ሂደት እንዲፈቱና በዚህም ሂደት የተረጋጋ ማህበረሰብ ለመፍጠር እድል ይሰጣቸዋል። ከዚያም በተጨማሪ ግን ይህንን ውይይት በፍፁም እንዳይንዛዛና ልቅ እንዳይሆን አስፈላጊ የሆነ አጥር ያበጅለታል። ከዚህ አንፃር ይህ ውይይት በተለይ የሚያተኩረው ሁሉም የዜጎችን እኩልነት በተቀበሉ ግን በአንድ በኩል በተለይ በዘውጌ ማህበረሰባት በደሎች ላይ በማተኮር በተደራጁ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ አይነት አደረጃጀት የእኩልነት መሰረት አይሆንም፤ እንዲያውም ለአድልዎ በር ይከፍታል፤ በተለይም ደግሞ ይህ ዘውጋዊ አመለካከት የአገርን አንድነት ያናጋል ብለው ከልባቸው በሚፈሩ ስለዚህም በግለሰብ መብት መከበር ዙሪያ መደራጀት ነው የሚበጀው ብለው በሚያምኑ ሀይሎች መሀል ያለው ልዩነት ላይ ያነጣጥራል።

**የፍተሻ ጥያቄ: እዚህ አዳራሽ ውስጥ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እኩል መሆን አይገባቸውም ብሎ የሚያምን አለ?**

ይህንን እሳቤ ከምር ከወሰድን ለዴሞክራሲያዊ ስርአት በጋራ መታገል አለባቸው የምንላቸው ሀይሎች በመሰረቱ የሰዎችን እኩልነት በተቀበሉት መሀከል ነው ማለት ነው:: የሰዎችን መሰረታዊ እኩልነት የተቀበሉ ሀይሎች ደግሞ መነሻ ኢላማው የሰዎችን እኩልነት የተቀበለና ይህንን እኩልነትም በህግ ፊትም ሆነ በፖለቲካው ተግባራዊ ለማድረግ ለሚንቀሳቀስ ስርአት አብረው የማይታገሉበት አሳማኝ የሆነና በግልፅ በህዝብ ፊት ለውይይት መቅረብ የሚችል ምክንያት አይኖርም::አብሮ በመታገል ግን የሚያገኙ ትን ጥቅም ለማሳየት በፍፁም አይከብድም::

የመጀመሪያው አሳማኝ ምክንያት የሚታገሉለት ስርአት ምንነት ነው:: በብሄር የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች እንታገላለን የሚሉት ለእኩልነት ነው:: በታሪክ የተፈጠረን የአድልዎ ስርአት ለማስወገድ ነው የምንታገለው እሰካሉና በአንፃሩ ይህንን የታሪክ አድልዎ ለማጥፋት እኛ አሁን በተራችን አድልዎ መፈፀም አለብን እስካላሉ ድረስ የሚታገሉት ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ነው ማለት ነው:: ጥያቄው ባህላችን ይጠበቅልን፤ ቋንቋዎችን ይደግልን፤ አካባቢያችንን እራሳችን በመረጥናቸው የአካባቢው ነዋሪዎች እናስተዳድር፤ የአካባቢያችንን ኢኮኖሚ እናልማ እስከሆነ ድረስ፤ መልሱ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ውስጥ የተካተተ ነው ማለት ነው:: በግለሰብ መብት ዙሪያ የተሰባሰበው የፖለቲካ ሃይል የሚጠይቀውም ይህንንው የዴሞክራሲያዊ ስርአት ነው:: እንደ ግለሰብ የመናገር፤የመፃፍ፤ የፈለግሁትን የማምለክ፤ በአገሬ ውስጥ የመረጥኩበት ቦታ ተዘዋውሬ የመስራት፤ ባለሁበት በመኖሪያዬ አካባቢም ሆነ በአገሬ የሚያስተዳድረኝን መንግስት የመምረጥ መብቴ ይጠበቅ፤ እኔ ባልመረጥኩት ማንነቴ መበደል የለብኝም፤ ከሌሎች ዜጎች ጋር በእኩልነት መታየት አለብኝ እስከሆነ ድረስ ጥያቄው የዴሞክራሲያዊ ስርአት ጥያቄ ነው:: በሁለቱ ሀይሎች ማለትም የግለሰብና የወል መብት መከበር ጥያቄ በሚያነሱት ወገኖች (ሃይሎች) መሀከል ሊኖር የሚችል ማንኛውም ልዩነት በመሀከላቸው ካለው የአላማ መቀራረብ ጋር ሲነፃጸር ኢምንት ነው ማለት ይቻላል::

በአጭር ጊዜም ሆነ በረጅም ጊዜ ሚዛን እነኝህ ሀይሎች ለየብቻቸው በምንም ስም ከሚመጣ አምባገነንነት ጋር ያላቸው ልዩነት በመሀከላቸው ካለው ልዩነት ጋር ሲመዘን እጅግ የገዘፈ ነው:: የሂትለር አምባገነንነት ለሌላው (ጀርመንኛ ለማይናገረው) የአለም ህዝብ እጅግ አሰቃቂ ቢሆንም ለጀርመን ህዝብም የከፋ ስርአት መሆኑ አያጠያይቅም:: ጀርመኖቹ ያተረፉት በስማቸው በሚደረግ ጦርነት ማለቅ፤ ለረጅም ጊዜ ባገራቸው ሰዎች አረመኔያዊነት ማፈር መሳቀቅና አንገታቸውን መድፋት ብቻ ነው:: ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በሁዋላ በጀርመን ዴሞክራሲያዊ ስርአት ተመስርቶ እድሜ ልኩን ሲወጋው ከነበረው የፈረንሳይ ህዝብ ጋር ያለምንም ድንበር የአንድ የአውሮፓ ማህበረሰብ አባል ሆኖ በሰላም ሲገበያይና ሲኖር ላየ የዛሬው ትውልድ ጀርመናዊ (ጥቂት ካበዱት አዲሶቹ ናዚዎች በስተቀር) የነሂትለርን እብደት እያሰበ ይዘገንነው እንደሆነ እንጂ «ጀግናዎቹ ያገሬ ልጆች» ብሎ ሲመፃደቅ መገመት አይቻልም::

ከዚያም በላይ ግን ዴሞክራሲያዊ ስርአት የሚፈጥረው የነፃነት መንፈስ በጋራ ለማደግ ከሚፈጥረው እድልም በተጨማሪ ሁሉም በየበኩሉ ለማደግ የሚያደርገውን ጥረት ስለሚያበረታታ በማህበረሰቡ ውስጥ አሉታዊ የሆነ መቃቃርን ይቀንሳል:: ፉክክርም ቢኖር በአድልዎ ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን ማህበረሰቡ እስከተገነዘበ ድረስ (እንዲህ አይነት አድልዎ እንዳይኖር በህግ ስለሚቆጣጠር) አልባሌ የሆነ የቅናትና የምቀኝነት ስሜት ከመፍጠር ይልቅ ጤናማ የሆነ የውድድር ስሜትን በመፍጠር አንዱ ከሌላው የሚማርበትን ሁኔታ ይፈጥራል:: እንዲህ አይነት አወንታዊ ስሜት እየተጠናከረ ሲመጣ ደግሞ የአሁኑን የአብሮነት ኑሮ ማሻሻል፤ የወደፊቱን ትውልድ ህይወት ከጥላቻ ማራቅ ብቻ ሳይሆን በተወሰነ ደረጃም የታሪክን ጠባሳም የማሻር ሀይል ያለው ይመስለኛል:: በሌላ አነጋገር ዴሞክራሲያዊ ስርአት ከፖለቲካ አስተዳደር ትክክለኛነቱ በተጨማሪ የከረሙ አጉል ባህሎችን በተሻለ የጋራ ባህል የመለወጥ አቅምም ያለው፤ በሀይል ሳይሆን ቀስ በቀስ በመረዳዳት ማህበረሰቡን በጣም የማቀራረብ ችሎታ ያለው ስርአትም ነው:: እነኝህ በጥቂቱ የጠቀስኩዋቸው የዴሞክራሲያዊ ስርአት በጎ ጎኖች በራሳቸው ትግልን ለማስተባበርና ይህንን ስርአት በቶሎ ለማምጣት ሁሉንም ሀይሎች በማጉዋጉዋት ወደ ጋራ ትግሉ ሊያሰባስባቸው ይገባል::

ከስርአቱ መመስረት በሁዋላ ሁሉም የሚያገኘው ጥቅም መኖሩ ብቻውን ግን አይደለም ትግሉን ለማስተባበር ሊገፋፋን የሚገባው:: እዚያ ቦታ በአጭር ጊዜ ለመድረስ የሚያስችለንም ይኸው የጋራ ትግል መሆኑ ነው:: አምባገነናዊ ስርአቶች ባጠቃላይና እንደነመለስ ማህበረሰቡን በየፈርጁ በመክተፍ መለያየትና እርስ በእርሱ ማባላትን እንደ ታላቅ የፖለቲካ እውቀት አድርገው የሚመፃደቁ ወሮበሎች በሚገዙት አገር የባላንጣን የተበላ ስልት እያወቁ እሱን ለማክሸፍ ተግቶ አለመስራት ፍፁም ምህረት የማይደረግለት ስህተት ነው የሚሆነው:: እነሱ ለእኩይ ተግባራቸው ተግተው ሲሰሩ፤ ብዙ ንብረት ሲያፈሱ፤ እኛ ቢያንስ ለበጎ ነገር ጉልበታችንንና እውቀታችንን ማዋል ሊያቅተን አይገባም:: ይህ ለምን እንደሚከብደን በሁዋላ እመለስበታለሁ:: ለአሁኑ ግን በጋራ መታገል ሀይላችንን በማስተባበር፤ የአንዳችንን ድክመት አንዳችን እየሸፈንን፤ የትግላችንን ማህበራዊም ሆነ ጂኦግራፊያዊ አድማስ በማስፋት ስለሆነም በባላንጣችን በቀላሉ ባለመጠቃት፤ በባላንጣችን በራሱ ውስጥ መሰነጣጠቅን በመፍጠርና በማዳከም...ወዘተ ወደ ድላችን እንደሚያቀርበን የምንስማማ ይመስለኛል:: እንዲያውም እንደዚህ አይነት በመርህ ላይ የተመሰረተ የጋራ ትግል የተጀመረ እለት የመለስ የበረከትና የስብሀት መንግስት የቆመበት መሬት እንደሚከዳውና በቀላሉ ሊፍረከረክ እንደሚችል ብዙ የሚያጠራጥር አይመስለኝም::

በጋራ ትግል ሂደት የሚገኙ ብዙ ዘላቂ ጥቅሞችም አሉ:: ከላይ የጠቀስኩት ሁላችንም የምንፈልገው የዴሞክራሲያዊ ስርአት በአንድ ሀይል ጥረትና ጉልበት ከሚመጣ በስርአቱ ምንነት ላይ በተስማማ የጋራ ትግል መምጣቱ ስርአቱን የበለጠ የተረጋጋና ዘላቂ ያደርገዋል:: በስርአቱ ምንነት ላይ ቀድመው የተስማሙና የስርአቱን ፍላጎት ከራሳቸው ጥቅም ጋር ያዛመዱ

የተለያዩ ሀይሎች በአንድ ላይ ታግለው የሚያመጡት ድል በማንም ብቸኛ ሀይል እንዳይቀማ ለመከላከል ስለዚህም ስርአቱ በጮርቃነቱ ክፉኛ እንዳይጎዳ ለመጠበቅ ይቻላቸዋል:: ከዚህ በተጨማሪም ግን በትግሉ ሂደት የሚኖር መተዋወቅ፤ እያደር የሚመጣ መተማመን፤ እየደነደነ የሚሄድ በአላማ አንድነት ላይ የተመሰረተ ጉዋዳዊ ስሜት፤ አብሮ ችግር በመቅመስ የሚመጣ የሌላውን ህመም የመጋራት ፍላጎት ተደማምረው ቀድመው የነበሩትን የመጠራጠርና ያለመተማመን ስሜት እየሸረሸሩት ሄደው ጥልቀት ያለው በነፃነትና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የዜግነት አገራዊ ስሜት ለማዳበር ሁኔታውን ያመቻቻሉ::

እነኚህን የዴሞክራሲያዊ ስርአት ፍሬዎች በጋራ ለመሰብሰብ እንዲቻል ግን በዚህ ትግል ውስጥ የሚሰባሰቡ ሀይሎች በዴሞክራሲያዊ ስርአት መፈጠር፤ በዚህ ስርአት መንፈስም መስማማት ይጠበቅባቸዋል:: ትብብሩ የሚመሠረተው በጊዜያዊ የፖለቲካ ስልጣን ቁማር ላይ የተመሰረተ ትብብር ሳይሆን እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ለመመስረት ከመጣ ቁርጠኝነት ሊሆን ይገባዋል:: ከዚያም በተጨማሪ ለእንዲህ አይነት ትብብር መሰረት የሚሆነው ሁላችንም የአንድ በፍትህና በዴሞክራሲ ስርአት ለይ የተመሰረተ የፖለቲካ ማህበረሰብ አካል ነን ብቻ ሳይሆን ህይወታችን፤ የወደፊት እጣ ፈንታችን በፅኑ የተቆራኘ መሆኑን ከልባችን ስናምን ብቻ ነው እንደዚህ በጋራ በተግባር ለመታገል ብቻ ሳይሆን ቁም ነገር ያለው ውይይት እንኳዋን ማድረግ የምንችለው:: በነኝህ ሁለት የማእዘን ድንጋዮች ላይ በመመስረት ነው እንዲህ አይነቱን የጋራ ትግል ማሰብ የምንችለው::

### 3. ለምን ለዴሞክራሲ የጋራ ትግል ማድረግ አልተቻለም?

ከላይ የጋራ ትግልን ጠቃሚነትና አስፈላጊነት በሚመለከት ያቀረብኩት አወንታዊ ትንተና የሚቀርብበት መቃወሚያ የሀሳቡ ትክክለኛነት ላይ አይደለም:: የኢትዮጵያ የዘመናዊ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ እንደ መተባበር ብዙ የተባለለት ግን በተግባር በፍፁም ሊውል ያልቻለ ፅንሰ ሀሳብ ያለ አይመስለኝም:: ፈረንጆች በእኔ ሙያ ሲቀልዱ ሁለት ኢኮኖሚስቶችን አንድ ጥያቄ ብትጠይቃቸው ሶስት መልስ ታገኛለህ እንደሚሉት፤ እኛም ኢትዮጵያውያን ላሉብን የፖለቲካ ችግሮች ሁላችንም በየግላችን የምንሰጠው መልስ ብቻ እውነተኛው መልስ ይመስለናል መሰለኝ ትንሽ ትንሽም ሆነን የራሳችንን ቡድን መፍጠር ይቀናናል:: የበለጠ የሚገርመው ግን የየራሳችንን ቡድን መፍጠራችን ብቻ ሳይሆን ቡድኑን ከፈጠርንም በሁዋላ ከሌሎች ቡድኖች ጋር የሚኖረን ግጭት እያደር እየከረረ እንጂ እየተቀራረበ ሲሄድ እምብዛም አይታይም:: ትንሽ ከቆየም ዋናው ባላንጣ ማን መሆኑን ሁሉ ያዘነጋናል:: ለማንኛውም ከላይ ያቀረብኩት አብሮ

የመታገል ፍሬ እውን እንዲሆን በመጀመሪያ እስከአሁን በዘውግ በተደራጁና ዘውግ ዘለል በሆኑ ሀይሎች መሀከል እውነተኛ ትብብር ለመፍጠር ለምን አልተቻለም? የሚለውን አከራካሪ ጥያቄ በመጠኑ ለመመለስ ልሞክር::[4]

በመጀመሪያ ግን መረዳት ያለብን ጉዳዩ የተለያዩ አይነት ምክንያቶችን ያቀፈ እንደመሆኑ በእንዲህ አይነት አጭር ንግግር ሁሉንም ለመንካት አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን እንደዚያ አይነት በተለይ የከዚህ በፊቱ ሙከራዎች የገጠሙዋቸውን ድርጅታዊ፤ባህላዊና አንዳንዴም ከግለሰቦች ፀባያት ጋር የተያያዙ እንቅፋቶችን ለመተንተን የሚያስችል ዝርዝር እውቀቱም የሌለኝ መሆኑን ነው:: ለተነሳሁበት የዚህ ፅሁፍ አላማም ብዙ አይጠቅመኝም:: ይልቁንም ትርፋማ የሆነ ውይይት ይሆናል ብዬ የማተኩርበት እነዚህ ትግሎች በሀሳብ ደረጃ ገንነው በወጡበት ጊዜ የነበሩትን አንዳንድ ገዢ አስተሳሰቦች በመመርመር ከነኝህ ሀሳቦች ጋር የተያያዙ ችግሮች እንዳሉ ለመመልከት ነው የምሞክረው::

ዘላቂነት ያለው በመርህ ላይ የተመሰረተ የትግል አንድነት ለመፍጠር ህብረቱን በሚመሰርቱ ሀይሎች መሀከል ስለ ትግሉም ሆነ ከትግሉ በሁዋላ ስለሚመሰረተው ስርአት ግልፅ መናበብ ያስፈልጋል:: እንዲህ አይነት መናበብ እንዲኖር ደግሞ በመጀመሪያ ሁሉም እራሱ የቆመበትን መሬት በደንብ መመርመር ያለበት ይመስለኛል:: እንዲህ አይነቱን ምርመራ በሁለት ከፍለን ማየቱ ይጠቅማል:: የመጀመሪያው በሁለቱም በኩል ያሉ የፖለቲካ ሀይሎች የሚጋሩዋቸው (የአንድ አጠቃላይ የፖለቲካ ባህል ውልዶች ስለሆኑ) በቀጥታ ከፍሬ ነገሩ ጋር ያልተያያዙ የፖለቲካ ጠባዮች (attitudes) ሲሆኑ ሁለተኛው በቀጥታ ከአቋዋም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ናቸው:: በየተራ እንመልከታቸው::

የኢትዮጵያውያንን ፖለቲካ ለፊቺ እንዲያስቸግር ከሚያደርገው ነገር አንዱ ስለፖለቲካ ያለን አመለካከት ነው::[5] በመጀመሪያ በስፋት የሚታየው ፖለቲካ ያለውን ሁሉ ዘርግፎ እንደሚያስይዝ ቁማርተኛ ሁሉም ወይንም ምንም የሚል አይነት ነው:: ቀስ ብሎ የሚያድግ የለዘብተኛ ፖለቲካ ባህል አላዳበርንም:: ከዚህ ጋር የተያያዘው አሸናፊ ሁሉን የሚያሸንፍበት፤ ተሸናፊ ሁሉን የሚያጣበት ጨዋታ ተደርጎ ነው የሚወሰደው:: ስለዚህም በተለይም ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ የግድ ከሚለው ሁሉም ሊያሸንፍበት ከሚችል ድምሩ ከዜሮ በላይ የሆነ ጨዋታ ተደርጎ አይወሰድም:: ይህ የፖለቲካ ልምድ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ፖለቲካ ጥርሱን

[4] ይህ ማለት ከዚህ በፊት በህብረ ብሄርና በብሄር በተደራጁ ሀይሎች መሀከል የትግል ህብረት አልተፈጠረም ለማለት አይደለም:: እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሀይሎች ህብረት እንደነዚህ አይነት ድርጅቶችን አቅፎአል:: ይህ ግን በዋና ዋና የብሄር ድርጅቶችና በህብረ ብሄራዊ ድርጅቶች መሀል የፀናና ቀጣይነት ያለው፤ በመርህ ላይ የተመሰረተ ህብረት ሊፈጠር አለመቻሉንና ይህም ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ክፉኛ መጉዳቱን ሊያስክደን አይችልም::

[5] እነኝህ የምጠቅሳቸው ጉዳዮች ሁሉንም በፖለቲካ የሚሳተፉ ሰዎችን ይመለከታል ማለት እንዳልሆነ አውቃለሁ:: በአጠቃላይ ፖለቲካችን የዚህ ችግር አለበት ማለት አጠቃላይ አቅጣጫውን ለማመላከት ያክል ነው:: ከነኝህ አይነት ችግሮች ነፃ የሆኑ ግለሰቦች መኖራቸውን ለመካድ አይደለም::

ከነቀለበት የግራ ፖለቲካ የተወሰደ ነው የሚል ግምት አለኝ:: አንዳንዶች ይህ አመለካከት ከፖለቲካችንም ባለፈ በሌላው ህይወታችንም ስር የሰደደ ባህል ነው ይላሉ:: ይህ ከሆነ ፈተናው ቀላል አይደለም:: ለማንኛውም ግን ለዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ መጠንከርም ሆነ እሱን ለማምጣት ለሚደረግ የጋራ ትግል ይህ ባህል መቀየር አለበት:: ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ በተፈጥሮው የሰጥቶ መቀበል ፖለቲካ ነው:: ይህ ድምሩ ዜሮ የሆነ የፖለቲካ ባህል ደግሞ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በፖለቲካ የሚለዩንን ከምናይበት መነፅር ጋር የተያያዘ ይመስለኛል:: ከኛ የተለየ አስተሳሰብ ያለው ሰው በተለያየ ምክንያት ይህ አመለካከት ለጋራ ህይወታችን የበለጠ ይጠቅማል ብሎ አምኖ (በትክክልም ሆነ በስህተት) ሊይዘው ይችላል ብለን ከማሰብ ይልቅ አውቆ፤ እኛን ለመጉዳት ወይንም ራሱን ብቻ ለመጥቀም ብሎ የያዘው ነው ብለን ማመን ይቀናናል:: ይህ አመለካከት ሁሌም ስህተት ነው ማለት አይደለም:: ግን ሁሌም ትክክል አይደለም:: የዚህ አይነት አመለካከት ቀና ውይይት የሚፈልገውን የሌላውን ሀሳብ እሱ ካየበት ጠገግ ለማየት መሞከርና በዚህም የራስን አመለካከት እንደገና የመመርመርን ጤናማ አካሄድ ያሰናክልና ሁሉም በያዘው አቋዋም ቸክሎ አልነቃነቅ እንዲል ይገፋፋዋል:: በዚህ አይነት የስንፍና አካሄድ ደግሞ ሩቅ መሄድ አይቻልም:: ስለዚህም ለዴሞክራሲያዊ ስርአት የሚመቸው አካሄድ በመጀመሪያ ለሌላው ሰው አመለካከት የሚገባውን ቀናነት ሰጥቶ በምክንያታዊነት መመዘኛ ተቀባይነት ሊያገኝ መቻል አለመቻሉን፤ ይህ አመለካከት እራሳችን ከያዝነው አመለካከት ጋር ሲመዘን ሙሉ ለሙሉ እንኩዋን ባይሆን ከፊል እውነት ሊኖረው ይችል እንደሆን መመርመር፤ ለሰውየው ከምክንያታዊነት ውጪ ያለ ሌላ ፍላጎት ከማልበሳችን በፊት መውሰድ ያለብን ቀዳሚ እርምጃ ይሆናል::

ይህ ግን መቀራረብን ለመከልከል ከአመለካከት በላይም ፋይዳ አለው:: አንድ ሰው የያዘውን አመለካከት አቅጣጫ የሚሰጡት ብዙ ምክንያቶች ናቸው:: በደንብ የማያውቁትን ነገር መፍራትና መጠራጠር ከአውሬነታችን የወረስነው የደመነፍስ ባህርይ ነው:: አመለካከታችን በተወሰነ ደረጃ ይህንን ያንፀባርቃል:: ሴትየዋ ከእንዲህ አይነት ፍርሀት በመነሳት ከሆነ ያንን አቋዋም የምታንፀባርቀው፤ በቂ ጆሮ ሳይሰጡ አቋዋሙን ማናናቅና ማጣጣል አቋዋሙን በመጀመሪያም የፈጠረውን ፍርሀት የበለጠ ያባብሰው ስለዚህም አቋዋሙን ያደነድነው እንደሆነ እንጂ አቋዋሙን አስትቶ ወደትክክለኛው መንገድ አይመራውም:: አንድ ሰው አቋዋሜ ትክክለኛ እስከሆነ ድረስ ምን ቸገረኝ፤ ሌላው ሰው በስህተቱ ይቀጥልና ውጤቱን ያገኘዋል ብሎ ሊተወው ይችላል:: ይህ ግን ፍፁም የግል የሆነ ህይወት ላይ ብዙ ለውጥ ላያመጣ ይችላል:: በጋራ የፖለቲካ ህይወት ላይ ግን ተደማምሮ የሚጭረው እሳት ሁሉንም መለብለቡ አይቀርም:: ሌላ ቢቀር ግን ከላይ ላልነው ሁላችንንም ለሚጠቅም የወደፊት ህይወት ግንባታ አያግዝም:: የሌላውን ፍርሀትና ጭንቀት ከልብ ለመረዳት መሞከር፤ ተረድቶም ከፍርሀቱና ከጭንቀቱ እንዲወጣ ማገዝ በተራ ሰብአዊነትም ተፈላጊነት ያለው ሌላ ቢቀር ያፀድቃል ብለው ሁሉም

ሀይማኖቶች የሚመሰክሩለት ነውና ያንን ቀና መስመር መከተሉ ይመረጣል:: ይህ ማለት ግን አንዳንድ ሰዎች እንደሚፈሩት ይህ አካሄድ ከሌላው (በተበደልኩ ስም) ግፍን ለመቀበል የሚያስችል ጫንቃ እንዲኖረን ለመስበክ በፍፁም አይደለም:: ይልቁንም ግፍን ለመቋቋቁዋም የምንወስደውን እርምጃ የጠራና እራሱን ከሌላ ግፍ መስራት ያፀዳ በማድረግ ያጠናክረዋል እንጂ:: የዚህ አካሄድ ትልቁ ጥቅም በቀና ውይይት የጋራ መፍትሄ ለመፈለግ እንቅፋት የሆነብንን የጠለቀ የጥርጣሬ መንፈስ ቀስ በቀስ በመለወጥ ወደ እውነቱ፣ ወደ መፍትሄው እንዲያስጠጋን ነው:: እነኝህ ከላይ ያነሳሁዋቸውን አይነት ሌሎች ብዙ ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል:: ሁላችሁም በየቤታችሁ ብታስቡበት የዚህ አይነት ብዙ እንቅፋቶች የሚታያችሁ ይመስለኛል:: ለማሳየት ለፈለግሁት ነጥብ ግን በቂ ይመስለኛል:: እንደነኝህ አይነት ከአቁዋሙ ቁምነገር ጋር በቀጥታ ያልተያያዙ ግን ሁሉን ነገር የምንመዝንበትን ሚዛን የሚያዛቡ የአመለካከት ባህሎች ለጋራ ትግል እንቅፋት ሊሆኑ እንዴት እንደሚችሉ በበቂ ያሳየሁ ይመስለኛል:: በነኝህ ሀሳቦች ላይ በመጠኑም ቢሆን ከተረዳዳን በቀጥታ በአቁዋም ላይ የሚነሱ ጥያቄዎችን መመርመር እንችላለን::

በአቁዋም ደረጃ በግልፅ ወጥተው የሚነገሩት ጥያቄዎች መሰረታዊ ቢሆኑም በጣም ብዙ አይደሉም:: በሚገርም ሁኔታ ግን አቅዋሞቹ ራሳቸው በ1960 ዎቹ ተይዘው ከነበሩበት ብዙም ፈቀቅ ያላሉና በአብዛኛው ርዕዮተ አለማዊ ጥግ ይዘው በየጊዜው በአገራችን፣ በአካባቢያችንም ሆነ በአለማችን የሚቀያየሩትን ሁኔታዎች ከግምት በማስገባት ህይወት ያለው ውይይት እንዲደረግ የሚጋብዙ አይደሉም:: አንዳንድ ጊዜ በተግባር ለመፍታት የምንሻው ችግር መሆኑ ቀርቶ እንደ ሀይማኖት የቀኖና ክርክር ትክክለኛው መስመር ካልለየ በቀር ምንም ወደፊት መሄድ የማይቻል ሆኖ ይቀርባል:: እኔ የማቀርባቸው የክርክር ጭብጦች ይህንን አካሄድ ይሽሻሉ:: መነሻ እሳቤዬ ከዘውግ ጋር የተያያዙ ችግሮች በተግባር መፈታት ያለባቸውና ሊፈቱም የሚችሉ ተጨባጭ ችግሮች ናቸው ብሎ ስለሚነሳ የውይይቴም ትኩረት እዚያ ላይ ነው የሚሆነው::

ከትልቁ ጥያቄ እንነሳ:: የዘውጌ ማህበረሰባት መብቶች ምንድን ናቸው? እስከምን ድረስ መሄድ ይገባቸዋል? በተለይም ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ የራስን አገር እስከማቋዋቁዋም ድረስ ሊደርስ ይችላል ወይ? ወይንም ይገባል ወይ? የሚለው ትልቁ የመለያየት ብቻ ሳይሆን ያለመተማመን ምክንያት ነው:: ይህን ጥያቄ በመርህ ደረጃ ማንሳቱ ብዙም የሚጠቅም አይመስለኝም:: አንድ ዘውጌ ማህበረሰብ ይህንን መብት ለማግኘት መድረስ ያለበት ደረጃ ምን መሆን አለበት በሚል የስታሊንን አምስት ትንግርታዊ መስፈርቶች መሙዋላት አለመሙዋላታቸውን ስናሰላ ያጠፋነው ጊዜ ለተጨባጭ ችግሩ መፍትሄ በመፈለግ ብናጠፋው ኖሮ ይህ ችግር እስከአሁን አይከተለንም ነበር::

መገንጠል እንደመፍትሄ ሆኖ የቀረበው በተጨባጭ ላለ፣ ውጤቱ ለሚታይና ለሚሰማ በደል ወይም የመበደል ስሜት ነው፡፡ ለችግሩ መፍትሄ ከፈለግን በመጀመሪያ መመለስ ያለብን የተባለው በደል መኖር አለመኖሩ ላይ መስማማት ነው፡፡ ይህንን ጥያቄ ግን መመለስ ያለብን መልሱ ይዞ ሊመጣ የሚችለውን መፍትሄ ከወዲሁ በማሰብ ሊሆን አይገባም፡፡ ለመፍትሄ ፍለጋው እንቅፋት ነው የሚሆነው፡፡ ለምሳሌ በደል መኖሩን እያወቀ በደል አለ ካልኩ የሚጠየቀውን መፍትሄም መቀበል ይኖርብኛል ከሚል ምንም በደል አልነበረም ብሎ መከራከር የተበደለውን ሰው ስሜት ከመጉዳቱ በተጨማሪ ተበዳዩ ከዚያ ሰው ጋር ስለበደሉ በመነጋገር ለሁለቱም የሚበጅ መፍትሄ የመፈለግ እድሉን ይቀጨዋል፡፡ በአንፃሩ በደል መኖሩ የታመነለት ሰው የጋራ መፍትሄ ለመሻት ያለውን ፍላጎት ይጨምርለታል፡፡ የሌለውን በደል አለ የሚል ወይንም ትርፍ አገኝበታለሁ ብሎ የበደሉን ጥልቀት ከእውነት አርቆ እጅግ ያገዘፈ ሰው ከሌላው የሚያስፈልገውን አዛኝነት እንዳያገኝ ያደርገዋል፡፡ ለዚህ ነው የበደሉን መኖር አለመኖር እንዲሁም የጥልቀቱን መጠን ለእውነቱ በተጠጋ መልኩ ለማወቅ መሞከር የሚጠቅመው፡፡ በእኔ እምነት በኢትዮጵያችን ታሪክ ሂደት የነበሩት የአገዛዝ ስርአቶች እስከአሁንም ድረስ በተለያዩ ዘውጌ ማህበረሰባት ላይ የተለያየ ደረጃ ያለው በደል ማድረሳቸውን መቀበል ሀቀኛነት ከመሆኑም በላይ ወደ መፍትሄው አንድ እርምጃ ያቀርበናል፡፡ ይህንን ደግሞ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ፅኑ እምነት ባላቸው ሀይሎች ዘንድ ሲሆን የመፍትሄውን ጉዳይ ለብቻ ለይቶ ለማየት ይረዳል፡፡

በአንፃሩ በደል ነበር ብሎ መቀበል የበደሉ አድራጊ ላይ ስምምነት አለ ማለት አይደለም፡፡ ብዙ ጊዜ በጣም የሚያከራክረውና በደል መኖሩን ራሱን እስከመካድ የሚያደርሰው በተለይ ተበዳዮች በዳዮቻቸውን ወይንም የበደላቸውን ምንጭ አጥርተው ካለማወቃቸው የሚመጣ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከችግሩ አይነት ጋር የተያያዘም ነው፡፡ በመጀመሪያ በአንድ በተወሰነ ወቅት፣ በተወሰኑ ሰዎች ላይ፣ የተወሰኑ ሰዎች ያደረጉት በደል ሳይሆን የሚወራው አጠቃላይ የታሪክን ወቅት የሚመለከት ስለሆነ በተጠቂነት የሚነሱትም ሆኑ በአጥቂነት የሚከሰሱት ጥቅል ማህበረሰቦች በመሆናቸው በተለይ በግለሰብ ደረጃ ያጠፋም ያላጠፋም በጋራ የሚወነጀሉበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡[6] ይህ ደግሞ በተለይ ከበደሉ የተጠቀሙ አሉ የሚል እንድምታም ስላለውና በሀቅ ግን ምንም ያልተጠቀመ ብቻ ሳይሆን በሌላ መልኩ እኩል የተጎዳ አጥቂ የተባለው ዘውጌ ማህበረሰብ አባል እንዲህ አይነቱን ተጠያቂነት ለመቀበል በጣም ይቸግረዋል፡፡ ሁለተኛ በአብዛኛ ው የችግሩ እምብርት ያለው አሁን ሳይሆን ታሪክ ላይ ነው፡፡ የፅሁፍ ታሪክ ከገዳማታ ውጪ ባልተንሰራፋበት እንደ ኢትዮጵያ አይነት አገር ደግሞ በታሪክ እውነታ ላይ ለመስማማት ያስቸግራል፡፡ ከዚያም በተጨማሪ ግን በክርክሩ የሚሳተፉት በደሉን በፈፀሙትና በተፈፀመባቸው መሀል ሳይሆን የእነሱ ተወላጆች በሚባሉት መሀከል ነው፡፡ በግለሰብ ተጠያቂነት ደረጃ ደግሞ

[6] እዚህ ላይ ለበደሉ በምሳሌነት የሚጠቀሱ የተለዩ ድርጊቶች የሉም ለማለት ሳይሆን፣ በደሉ የሚወራው በጥቅሉ፣ ሁሉንም ማህበረሰብ በሚመለከት እንጂ በአንድ የተወሰነ ሁኔታ የተጎዱ ሰዎችን አለመሆኑን ለማሳየት ነው፡፡

በወላጆች ድርጊት ልጆች ተጠያቂ የሚሆኑበት (ወላጆቹ አጥፍተዋል እንኩዋን ቢባል) ሁኔታ ከፍትህ አንፃርም ለመቀበል አስቸጋሪ ነው:: ስለዚህም በአብዛኛው ጊዜ ችግሩን ዝም ብሎ እንደሌለ መቁጠር የቀለለው አማራጭ ተደርጎ ይወሰዳል:: ይህ ግን ምንጩን ልንረዳው እንኩዋን ብንችል አሁንም የሰነፍ መንገድ ነውና ችግሩን ከመሰረቱ አይፈታውም::

በነገራችን ላይ የግራ ፖለቲካ መድረኩን በተቆጣጠረበት ወቅት ይህንን የተወሳሰበ ችግር በጣም ቀላልና ለተራው ተመልካች ሊገባ በሚችል፣ ግን ያንን ፖለቲካ ለሚያቀነቅኑት ጠንካራ ድጋፍን ሊያሰባስብ በሚችል መልክ ይመልሱታል:: የግራው ፖለቲካ በመሰረቱ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያለው ዋናው ቅራኔ የመደብ ቅራኔ ነው፣ (በከበርቴውና በላባደሩ፣ በገበሬውና በባለመሬቱ...ወዘተ) የበደሎች ሁሉ እናት በድሀውና በሀብታሙ መሀከል ያለው የኢኮኖሚ ብዝበዛ በደል ነው ብሎ ስለሚነሳ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ሌሎች በደሎች ሁሉ መኖራቸውን አምኖና ተቀብሎ፣ እንዲያውም እነኚያን በደሎች በፅኑ እያወገዘ፣ ሆኖም ሁሉም ተበዳዮች ለዋናው በደል ቅድሚያ እንዲሰጡ ያስገድዳል:: ከሁሉም ዘውጌ ብሄረሰባት የመጡ የዚህ ርዕዮተ አለም ተከታዮች በጋራ ሆነው የመደብ ጭቆናን እንዲታገሉና በጋራ ትግላቸውም የሚፈጥሩት የኮሙኒስት ስርአት መሰረታዊ እኩልነትን በመፍጠር ሁሉንም አይነት በደሎች እንደሚያጠፋ ቃል ይገባል:: ይህ አመለካከት በዳዮችንም በሚመለከት ግልፅ ኢላማ አለው:: ሁሉንም አይነት በደሎች የሚፈፅሙት በስርአቱ የሚጠቀሙት የገዢው መደብ አባላት ስለዚህም አገዛዙ ነው:: ያንን አገዛዝ መጣል ብቻ ነው መፍትሄው:: ከዚህ ውጪ በዘውጌ ማህበረሰብ አባላት በኩል የሚነሱ ዘውግ ተኮር ጥያቄዎች የመደብ ጥቅማቸውን ለማስከበር የሚሩዋሩዋጡ ከተበዳዩ ብሄረሰብ ከሆኑ «ጠባብ ብሄረተኞች» በዳይ ከሚባለው ብሄረሰብ የወጡ ከሆኑ ደግሞ «ትምክህተኞች» ይሆኑና በቀላሉ ለጥቃት ይመቻቻሉ::

የዚህ አይነት የተመቻቸና ቀላል ትንተና ግን ከኮሙኒስት ስርአት ተቀባይነት ማጣት ጋር አብሮ መውደቁ ብቻ ሳይሆን የመደብ ትግል ተቀባይነት ሲያከትም ሌሎች ቅራኔዎችን በበለጠ ሀይል ወደ መድረኩ ያመጣቸዋል:: በዚያ ትንተና መሰረት ላይ ተንጠላጥለው በስልጣን ላይ የወጡትና ስልጣኑን እንደማንኛውም የአገዛዝ ስርአት የዜጎችን መብት በመርገጥ በስልጣን ላይ የተቆናጠጡትን ሰዎች ለመጥቀም ለማዋል ሲሞከር የሚያመጣውን ፍፁም የሆነ የአስተሳሰብ ቀውስ እነ መለስና ስብሀት አገዛዛቸውን ተቀባይነት ለመስጠት ላለፉት 17 አመታት ያደረጉትን እጅግ አሰልቺና ፍሬ ቢስ ትንተና የተመለከተ ሁሉ ይታዘበዋል:: ለዚህም ነው በመጨረሻው እንዲህ አይነት አገዛዝ ራቁቱን ከወጣ አረመኔያዊ ጉልበት በስተቀር ለአጭር ጊዜም ቢሆን በሁለት እግሩ ሊያቆመው የሚችል የተቀባይነት መሰረት የማይኖረው::

የፖለቲካው መሰረት የሊበራል ዴሞክራሲ በሆነበት ሁኔታ ይህንን ጥያቄ እንዴት ብንቀርበው የተሻለ መግባባት ላይ ያደርሰናል የሚለውን ነጥብ ወደ ሁዋላ ላይ በአጭሩ እመለስበታለሁ::[7] ከላይ የጀመርነውን ውይይት ለመቋዋጨት ያክል ግን በደል መፈፀሙን ከተስማማን፤ የተፈፀመው በደል በታሪክ ሂደት የተፈፀመ መሆኑን ከተማመንን፤ ይኸ የታሪክ በደል አሁንም ሙሉ ለሙሉ መፍትሄ አለማግኘቱን ካወቅንና (በደርጉም ሆነ በዘረኛው አገዛዝ ወቅት የተካሄዱት የመሬት ሥሪትና የክልል ፖሊሲዎች የበደሉን አስከፊ ገፅታ ለመለወጥ ያደረጉትን አስተዋፅኦ ሳንክድ) በመግቢያዬ ላይ እንዳልኩት የወደፊቱ ፖለቲካችን ሁሉንም ዜጋ (በግለሰብም ሆነ በቡድን) በመብት ደረጃ እኩል መሆኑን ያለምንም ማመንታት ከተቀበልን፤ የበደሉ ምንጭና የበደሉ ጥልቀትን በሚመለከት ያሉትን በርግጥም አከራካሪ ጉዳዮች ለታሪክ ተመራማሪዎች ትተን ግን በደሉን በማወቅ የሚመጣውን ለሌላው ጭንቅ ሀዘኔታን የመስጠት አስፈላጊና አቀራራቢ ስሜት ተጠቅመን፤ ሁላችንም በጋራ ወደፊት የምንሄድበትን መንገድ ለመቀየስ ሊቸግረን አይገባም እላለሁ:: ይህ እንዲሆን ግን ከላይ እንዳልኩት ለጥርጣሬያችን መሰረት የሆኑትን እንቅፋቶች እንደዚህ በግልፅ አውጥተን ልንወያይባቸው ይገባል::

ወደሚቀጥለው ነጥቤ ከመሄዴ በፊት ግን አሁንም አንድ አከራካሪ ግን አስፈላጊ ጉዳይ ላንሳ:: የታሪክ በደሎች አንድን ማህበረሰብ ወደፊት ከመሄድ እንዳይከለክሉት ስለታሪክ የሚኖረን እይታ ትንሽም ቢሆን አምክህኖታዊ መሆን አለበት:: ሁሉም የታሪክ ክስተቶች መመዘን ያለባቸው በጊዜው በነበረ ሁኔታ እንጂ ዛሬ ከደረስንበት ስልጣኔ በመነሳት ሊሆን አይችልም:: አሁን ያለምንም ጥያቄ ስህተትና ነውር መሆኑን የምናምነው ነገር በጊዜው የነበረው ማህበረሰብ ነውር መሆኑን አውቆ ነው ያደረገው ወደማለት አይወስደንም:: እንዲያውም ጥሩ ነገር ነው ብሎ አምኖ ሊሆን ይችላል ያደረገው:: በእኛ የህይወት ዘመን ያየነው አንድ ቀላል ምሳሌ ልስጥ:: የሴቶች ግርዛት በአገራችን በአብዛኛው ዘውጌ ማህበረሰባት (በከተሞች ጭምር) ሲፈፀም የነበረ፤ እንደ ጥሩ ነገር ሲታይ የነበረ ነው:: ወላጆች ሴት ልጆቻቸውን ሲያስገርዙ ልጆቻቸውን ለመጉዳት ብለው እንዳልሆነ መቼም አንጠረጥርም:: ዛሬ ግን ይህ ባህል ሴት ልጆችን የሚጎዳ ብቻ ሳይሆን በአንዳንድ ቦታዎች ወላጅን በወንጀል የሚያስጠይቅ አስነዋሪ ድርጊት ተደርጎ እየተወሰደ ነው:: በተመሳሳይ በታሪክ የአገዛዝ ስርአቶች ብቃትና ችሎታ የሚታይበት ትልቁ መስፈርት የግዛት መስፋፋት ነበር:: (ዛሬ መብት ማክበር፤ ፍትህ፤ ብልፅግና ማምጣት የሆነውን ያክል) የግዛት መስፋፋት ደግሞ የሚደረገው በጉልበት፤ አሸናፊው ተሸናፊውን አስገብሮ ነው:: ይህ ደግሞ አላማው ሆን ብሎ ለመጉዳት እንኳዋን ባይሆን በተለይ በተሸናፊው ላይ ከፍተኛ በደልን ያደርሳል:: በሁሉም ቦታ ማለት ይቻላል በዚያን ዘመን አገሮች አገራዊ

[7] እዚህ ላይ አንባቢ ልብ እንዲልልኝ የምፈልገው የሊበራል ዴሞክራሲ የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ የምጠቀምበት ፖለቲካውን በሚመለከት ብቻ ወይንም እውቁ ፈላስፋ ጆን ራውልስ ፖለቲካል ሊበራሊዝም በሚል ለይቶ የሚጠቀምበትን ነው:: በዘመናዊው አጠቃቀም ሊበራሊዝም (በተለይም አዲሱ አይነት) ከዚያም ባለፈ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ፖሊሲ ዙሪያ ያለውን አመለካከት የሚያንፀባርቀውን አይደለም::

ቅርፃቸውን የሚይዙት በእንዲህ አይነት የመስፋፋት እንቅስቃሴ ነው:: የተለያዩ ሰዎች ወይንም ዘውጌ ማህበረሰባት ተሰብስበው በዴሞክራሲያዊ አካሄድ እጃቸውን አውጥተው የፈጠሩት አገር በታሪክ የለም:: ይህ የታሪክ ክስተት የጊዜውን እውነታ የሚያመለክት ከሆነ በጊዜው የነበረ አንድ ንጉስ ወይንም ገዢ ለመስፋፋት በመሞከር እንዴት ሊጠየቅ ይችላል? በመስፋፋት ወቅትም ለተፈጠሩ በደሎች ዛሬ ካለን አመለካከት ተነስተን በጊዜው የነበሩትን ገዢዎች እስከምን ድረስ ነው ተጠያቂ የምናደርጋቸው? ይህ ጥያቄ ሰፊ እንድምታ ያለው ጥያቄ ነው:: በአርግጥ የተፈፀመውን ግፍና በደል እንዳልነበረ አያደርገውም:: እንደዚያ ማህበረሰብ አባላትም በአንድ መልኩ ወይንም በሌላ የዚያ ታሪክ ወራሾች ነን:: በደሉ የተፈፀመበትን ሁኔታ ግን በተለየ ሁኔታ እንድናየው ይጋብዘናል:: ከዚህም ውስጥ ትልቁ አይንን ከሚጋርድ ጠንካራ ስሜታዊነት አውጥቶ፣ ታሪክን በታሪክነቱ ከስህተቶቻችን የመማሪያ መሳሪያ አድርጎ ወስዶ የዛሬን ትውልድ ግን የዛሬውን ችግር በመፍታትና ለወደፊቱ ትውልድ የተሻለ አለም ማስረከብ ላይ እንድናተኩር ያበረታታናል:: ተበድለናል የሚሉት ማህበረሰቦች አባላትም ቢሆኑ ሁለት መጠየቅ የሚገቡአቸው ጉዳዮች አሉ :: አንደኛው ታሪካዊ ወቅቱ በጠየቀው መሠረት የመስፋፋቱ አቀንቃኞች የራሳቸውም ማኅበረሰብ መሪዎች ሊሆኑ ይችሉ እንደነበር፣ የተለየ የፖለቲካም ሆነ የሞራል መሠረት ያልነበራቸው መሆኑንና ፤ ሁለተኛም የተስፋፊው ሃይል አስቀድሞ አቅሙን ለመገንባት የራሱ ማህበረሰብ ውስጥ የሚሰቀጥጡ በደሎችን በመፈፀም ሁሉን አይነት ተቀናቃኞችን ከደመሰሰ በሁዋላ ፊቱን ወደመስፋፋት ማዞሩን ታሪካዊ ግምት ማድረግ ይኖርባቸዋል :: ተዎድሮስ በሊማሊሞ አፋፍ እጅና እግራቸውን እየቆረጠ የወረወራቸውን ጎንደሬዎች ታሪክ ሳነበበ ፤ ወይም ሸዋ ውስጥ ፤

«አንተም ጨካኝ ነበርክ ጨካኝ አዘዘብህ

እንደ ገና ዳቦ እሳት ነደደብህ»

የተባለለትን የበዛብህን ጭካኔ ሳስተዋለ ፤ ተስፋፊው ማህበረሰብ ፤ አንድነት የጠየቀው ጭካኔ፣ የመጀመሪያው ገፈት ቀማሽ መሆኑን ሲያስተውል፣ ሃዘኔታ ሊሰማው ካልሆነ እሰይ ሊሰኝ እንደማይችል ግልፅ ነው :: እንዲህ አይነት የሀዘኔታ አስተሳሰብ ሲዳብርም ነው የትግል ህብረት ጉዳይ ዕውን መሆን የሚችለው ::

እንግዲህ እነኝህን ሁሉ ውስብስብ ጉዳዮች ከአእምሮአችን ሁዋላ አስቀምጠን ከላይ የጀመርነውን የመገንጠልን ጉዳይ በአጭሩ ልንመለከተው እንችላለን:: የታሪክ በደል ነበር ብለናል:: በተለያየ ቦታ በተለያየ ጊዜ፣ በተለያየ መጠን መብቶች ተጥሰዋል:: እንዲያውም ታሪካዊ የመብት መጣስን ሁላችንም የምንጋራው የታሪካችን ጠባሳ ነው:: የዚያ በደል ቅሪት በተወሰነ ደረጃ አሁንም አለ እንኩዋን ብንል እንዲህ አይነት በደል አሁን ባለንበት አለም ሊቀጥል እንደማይገባው ቢያንስ በመርህ ደረጃ ተስማምተናል:: ስለዚህ በዋናነት የሚነሳው ጥያቄ ይህ

በደል እንደገና በፍፁም እንዳይደገም የፖለቲካ ህይወታችንን እንዴት እናስኪደው የሚለው ነው:: ከዚያ ያነሰው ግን ተያያዥነት ያለው ጥያቄ ደግሞ ከዚህ በፊት በተፈፀመው በደል ምክንያት አሁን ባሉት ዜጎች መካከል የመወዳደሪያ ሜዳው ያልተስተካከለ ከሆነ ይህን ለማስተካከል ምን እናድርግ የሚለው ነው:: ይህ ደግሞ በጣም ተግባራዊ የሆነ፤ ከስሜተኛነት ካወጣነው የታሪክን ችግር ከዘመኑ ፍላጎት ጋር ባጣጣመ መልኩ በሰጥቶ መቀበል ድርድር ሊፈታ የሚችል ነው:: የመጀመሪያውን ጥያቄ ቀደም ብለንም በመርህ ደረጃ መልሰነዋል:: ከአሁን በሁዋላ የሚኖረን የጋራ ህይወት የሁላችንንም እኩልነት የተቀበለ፤ ፍትሀዊና ዴሞክራሲያዊ ስርአት በመፍጠርና ይህም እንዳይቀለበስ በጋራ በመጠበቅ እንመልሰዋለን:: ሁለተኛውን ጥያቄ በሚመለከትም ከሌሎች አገሮች ትምህርትን በመቅሰም የተበደሉ ወገኖች ፈጥነው ከሌላው ጋር ሊቀላቀሉ የሚችሉበትን አወንታዊ እርምጃዎች በመውሰድ (affirmative action) እንመልሰዋለን:: በጋራ መታገል የሚያስፈልገንም እንዲህ አይነቱን ስርአት ለመፍጠር ነው::

እንግዲህ የመገንጠል ጥያቄ በዚህ ሂደት የሚጨምርልን ምንድን ነው? ጥያቄውን ከሚያነሱት ወገን የሚሰማው ሁለት መከራከሪያ ነው:: አንደኛው እነኝህ በደሎች ተመልሰው ላለመምጣታቸው መከላከያ መድህን (insurance) ነው የሚል ነው:: ለዚህ ነው መገንጠሉን አሁን የማንፈልገውም ቢሆን በመብት ደረጃ መቀመጡ ይጠቅማል ብለው የሚከራከሩት:: ይህ ግን በእኔ አመለካከት በሁለት ምክንያት አሳማኝ አይደለም:: አንደኛው እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በሌለበት ይህን መብት በሕገ መንግስት ደረጃ ማስቀመጥ ምንም ዋስትና እንደማይሰጥ በአገራችንም ሆነ በሌሎች ኮሙኒስት አገሮች ያየነው ነው:: ይልቁንም የዚህ ስሜት መኖር ለእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት መመስረት ያለንን ቁርጠኝነት ጥያቄ ውስጥ ያስገባውና የዴሞክራሲ ሂደቱን ያሳሳዋል:: ሁለተኛው ይህ ነገር መኖሩ በራሱ በመሀላችን መተማመን እንዳይኖር ያደርገዋል:: ሁሉም ዘውጌ ማህበረሰባት የጋራ ህይወታቸው በጣም ጊዜያዊ የሆነና በምንም ጊዜ ሊቀየር የሚችል መሰረት የሌለው አብሮነት ያደርገዋል:: ከዚያም በተጨማሪ ግን ከአገራችን አንድነት ሁላችንም እንጠቀማለን ብለው የሚያስቡ አወንታዊ ሀይሎች ይህንን በአንድነታችን አንገት ላይ የተጠመጠመ ገመድ አድርገው ከመውሰድ በሚመጣ ቁጭት ለሁላችንም አስፈላጊ በሆነው የፍትህና የእኩልነት ጥያቄ ላይ በጋራ እንዳንዘምት ያዘናጋናል:: ይህም ያልተረጋጋ አንደነት ስሜት ክልላዊ ፤ ዘውገኛና አድሎአዊ ለሆኑ አሠራሮች ራሱን በማዋስ ፤ እርስ በርስ መጠላለፍ የበዛበት ፤ ተቀናቃኝነት የገነነበት ፤ ፖለቲካዊ ሥርአት በመፈጠር ራሱ የመለያየት ምክንያት ይሆናል ::

ሁለተኛው መከራከሪያ ግን እያንዳንዱ ዘውጌ ማህበረሰብ ተለያይቶ የራሱን መንገድ ቢቀይስ የተሻለ ሰላምና ዴሞክራሲ ለማምጣት ይቻላል የሚለው ነው:: ይህም የተሳሳተ እሳቤ መሆኑን ለማሳየት ከአካባቢያችንም መራቅ የለብንም:: በመጀመሪያ በአንድ ዘውጌ ማህበረሰብ ብቻ

የተፈጠረ አገር የተሻለ ሰላምና ዴሞክራሲ ለማምጣቱ ዋስትና የሚሆን ምንም ነገር የለም። ያ ቢሆንማ በአሁኑ ጊዜ በአለማችን ፍፁም የመተራመስ ምሳሌ የምትሆነው ከዘውግ አንፃር በአህጉራችን ሁሉ ንፁህ የምትባለው አገር ጎረቤታችን ሶማልያ አትሆንም ነበር። ወይንም ደግሞ በሰላምና በመረጋጋት እንዲሁም በመበልፀግ የሚታወቁት አገሮች የብዙ ዘውጎች መኖርያ የሆኑት እነ አሜሪካ፣ ስዊዘርላንድ፣ ካናዳ…ወዘተ አይሆኑም ነበር። በመገንጠል ሰላም ዴሞክራሲ ወይንም ብልፅግና የሚገኝ ቢሆንማ ኖሮ ኤርትራ የት በደረሰች ነበር። ከአለማችን ታሪክ እንደኩል ውሀ ጠርቶ የወጣው ነገር በአገሮች ውስጥ ሰላምና የተረጋጋ ኑሮ ለማምጣት በጣም አስፈላጊው ነገር በአገሩ ባሉ ህዝቦች ውስጥ ልዩነት አለመኖሩ አይደለም። ልዩነቶቻቸውን የሚፈቱበት ስልታቸው እንጂ። የመገንጠል ጥያቄ በደንብ ሳይብላላ እንደዚህ የፖለቲካ መድረኩ ውስጥ መግባቱ ግን ብዙ ችግሮች አሉት። ከእነኝህም ውስጥ ዋነኛው ከላይ በጠቀስኩዋቸው ምክንያቶች በዴሞክራሲያዊ ስርአት መመስረት በፅኑ የሚያምኑ ሀይሎች፣ በነመለስ የአምባገነን ስርአት በጋራ እየተደቆሱ ያሉ ሀይሎች ትግላቸውን አስተባብረው የሚፈልጉትን ስርአት ለማምጣት እንዳይችሉ ማድረጉ አልበቃ ብሎ ገዢዎች ሆን ብለው በሚፈጥሩአቸው የመከፋፈል እርምጃዎች አካባቢያችን በሙሉ የጥላቻ በሽታ የተስፋፋበት አሳዛኝ መንደር እንዲሆን አድርጎታል።

የመገንጠል ጥያቄን አንዴ ከውይይቱ ካወጣነው በሁዋላ የሚነሱት ሌሎች ጥያቄዎች ለመፍትሄ የሚያስቸግሩ ሊሆኑ አይገባም። የመገንጠልን ጥያቄ የሚቃወም ሰው በደልንና አድልዎን በመደገፉ ብቻ ነው ሊባል አይችልም። ከላይ ለማሳየት እንደፈለግሁት አድልዎን የሚቃወም መገንጠልም ለችግራችን መፍትሄ አይደለም እንዲያውም ወደባሰ ችግር ይከተናል ብለው ከልባቸው የሚያምኑ ቀና የፖለቲካ ሰዎች አሉ። በዚያው ልክ ደግሞ የመገንጠልን ጥያቄ በአካባቢያችን ለከት ላጣው በደል አፈናና እመቃ እንዲሁም ማባራት ያቃተው የጦርነት መአት መፍትሄ ነው ብለው ከልባቸው የሚያምኑ (እምነቱ የተሳሳተ እንኩዋን ቢሆን) ግን ይህን በማመናቸው ኢትዮጵያን የሚጠሉ ናቸው ሊባሉ የማይገባቸው፣ የተሻለ አማራጭ ለመመልከት ያልቻሉ ግን የሚፈልጉ ብዙ የፖለቲካ ሀይሎች አሉ። እነኝህ ሁለቱም ሀይሎች የነመለስ አምባገነናዊ አገዛዝ ሰለባዎች ናቸው። ሰብአዊ መብታቸው ተገፏል፣ ዴሞክራሲያዊ መብት የላቸውም። ሁሉም አድልዎ የሌለበት፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ፣ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ይመኛሉ። ቁጭ ብለው ተወያይተው ችግራቸውን የሚፈቱበት ሁኔታ ግን በአገራቸው አልተፈጠረላቸውም። ለእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በሚያደርጉት የጋራ ትግል ነው በእርግጥም ዘላቂ የሆነ መፍትሄ ሊያገኙ የሚችሉት። ለዚህም ነው እንደ ደመኛ ጠላት በጎሪጥ ከመተያየት ይልቅ ወደዚያ የሚወስደውን ውይይት ዛሬ ነገ ሳይሉ አሁኑኑ መጀመር አለባቸው የምለው። ለምክንያታዊነት ከተገዛን፣ አእምሮአችንን ብቻ ሳይሆን ልባችንን ከከፈትን፣ የሌላውን

ሀዘንና ስቃይ ለማድመጥና ለመራራት የሚያስችል አዛኝነት ካበለፀግን ከሚያራርቀን ይልቅ የሚያቀራርበን ምክንያት በጣም የበዛና የጠለቀ መሆኑን በቶሎ መገንዘብ እንችላለን እላለሁ፡፡

**4) የአዲስ አመለካከት አስፈላጊነትና ሁሉንም የሚጠቅም ስለመሆኑ (አዲስነቱ ለአገራችን ነው)**

ይህ እውን እንዲሆን ግን ከላይ ለጠቀስናቸው የአመለካከት ችግሮች ምትክ የሚሆን የአስተሳሰብ መሰረት ያስፈልገናል፡፡ ይህ የአስተሳሰብ መሰረት ምን መሆን እንዳለበት ከላይ በተለያየ ቦታ ጠቃቅሼዋለሁ፡፡ በአንድ ላይ ለመሰብሰብ ያክል ግን አንድ ሁለት ነጥቦችን ላንሳና ሁላችንም ለዚህ ሂደት በምን መልክ አስተዋፅኦ ማድረግ እንደምንችል ያሉኝን የተግባር ሀሳቦች አቅርቤ ላብቃ፡፡

በጣም በሚገርም ሁኔታ አሁን ባለው የኢትዮጵያ (የአለምም) የፖለቲካ ሁኔታ መሰረታዊ የሚባል የርዕዮተ አለም ልዩነት የለም፡፡ ሁሉም የሚያወራው አንድ አይነት ስርአት ለመመስረት እፈልጋለሁ እያለ ነው፡፡ ይኸውም በፖለቲካ መስኩ ከላይ የጠቀስኩት የሊበራሊዝም ሀሳብ ነው፡፡ የነመለስን ፍፁም መያዢያ መጨበጫ የሌለው እስታሊናዊ አምባገነንነትን «ከነጭ ካፒታሊዝም» ጋር ለማዋሀድ ከሚሞክረውና «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» የሚል የማደናገሪያ ስም ከተሰጠው «አመለካከት» ሌላ ማለቴ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን የዚህን ስርአት ምንነት በሚመለከት ግልፅ ግንዛቤ አለ ማለት አይደለም፡፡ በጉዳዩ ላይ ብዙ ያሰቡበትና የፃፉ ሰዎች እንደሚስማሙበት ይህ አመለካከት በዘመናዊ አቀማመጡ ቢያንስ የሚከተሉት ዋና ዋና ባህርያት አሉት፡

1) በመጀመሪያ የፖለቲካ ሊበራሊዝም[8] በአንድ በመሰረታዊ እምነቶች የሚለያይ ማህበረሰብ (ለምሳሌ በሀይማኖት፣ በባህል፣ በቋንቋዋ...ወዘተ) አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ (አገር) ሆኖ በሰላም፣ ልዩነቶቹን እያቻቻለ አብሮ ለመኖር የሚያስችለው የፖለቲካ ዘይቤ ነው፡፡ በምንም አይነት የሊበራል ፖለቲካ እነኝህን ልዩነቶች ለመፍታት ወይንም ለማጠጋጋት አይሞክርም፡፡ በዚህ ስርአት የአገር አንድነት ማለት እነኝህን ልዩነቶች ማጥፋት ማለት አይደለም፡፡ እነኝህን ልዩነቶች ይዞና እየተንከባከቡ ግን ከዚያ በላይ የሆነ በዜግነት ላይ የተመሰረተ የአገር አንድነትንና ካለፈም አገራዊ ብሄረተኝነትን ለማበልፀግ ነው የሚጥረው፡፡ ይህንን በቅጡ መረዳት በሁለት በኩል ጥቅም አለው፡፡ በአንድ በኩል ባህላዊ ስብስቦች በእንዲህ አይነት የፖለቲካ ማህበረሰብ ውስጥ በጥልቅ የምናምንበትና የማንነታችን መሰረት ነው ብለው የሚያምኑትን ባህላቸውን የሚያጡበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እነኝህ የባህል ስብስቦች የተለየ ባህላቸውን በማክበራቸው ወይንም አጥብቀው በመያዛቸው ምክንያት የአገሩን አንድነት እንደተፈታተኑ ተደርጎ

---

[8] በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ መፅሀፎች ተፅፈዋል፡፡ ለምሳሌ ያክል ግንይህን ጉዳይ በዝርዝር መመልከት ለፈለገ የጆን ራውልስን ኦን ፖለቲካል ሊበራሊዝም ወይንም የሮበርት ዳልን ሊበራል ዴሞክራሲ መመልከት ይችላል፡፡

በምንም አይነት ሊወሰድባቸው አይችልም፡፡ በባህል ጠንካራ አይሪሽ ሆኖም በዚያው ያክል የአሜሪካ ብሄረተኛ መሆን እንደሚቻለው ማለት ነው፡፡

2) የህዝብ ሉአላዊነት የማይገሰስ ነው፡፡ የዚያ የፖለቲካ ማህበረሰብ አባላት ሁሉ የሚተዳደሩት ህዝቡ በመረጣቸው መሪዎች ብቻ ነው፡፡ ይህ መሰረታዊ ዴሞክራሲያዊ መብት ለዜጎች ሁሉ በእኩልነት የተሰጠ መብት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ዜጎች ሁሉ በፖለቲካው መስክ እኩል ናቸው፡፡ አስተዳዳሪዎቻቸውን የሚመርጡት ደግሞ በሁሉም እርከን ለሚገኝ የመንግስት አካላት ሁሉ ነው፡፡ ያልተማከለ አስተዳደር የተቀላጠፈ የመንግስት አገልግሎትን ስለሚሰጥ የአካባቢ መንግስቶች እንደሁኔታው ያስፈልጋሉ፤ ስለዚህም በአገር ደረጃ ብቻ ሳይሆን የአካባቢያቸውንም መሪዎች የሚመርጡት እነሱው ዜጎቹ ናቸው፡፡ ዘውግ ብዙ በሆነና ዘውጌ ማህበረሰቦች በአንድ አካባቢ በሚኖሩበት ሁኔታም የአካባቢውን መሪዎች የሚመርጡት የዚሁ ዘውጌ ማህበረሰብ አባላት ናቸው ማለት ነው፡፡

3) ይህም ሆኖ ግን በህዝቡ የተመረጡ መሪዎችም ራሳቸው ሊሽሩዋቸው የማይችሉዋቸው ሰዎች በሰውነታቸው ይገባቸዋል ተብሎ የሚታመን መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች አሉዋቸው፡፡ እነኝህ የመናገር፤የመፃፍ፤ የዕምነት፤ የመሰብሰብ፤ በአገራቸው ከቦታ ቦታ ያለምንም ማዕቀብ የመዘዋወርና የመስራት...መብቶች በየትኛውም እርከን ያለ መንግስት ሊሽራቸው የማይችሉ መብቶች ናቸው፡፡

4) የህግ የበላይነት የተረጋገጠ ነው፡፡ አስተዳደር በዘፈቀደ ሳይሆን ለሁሉም ግልፅ በሆነና ሁሉንም በእኩልነት በሚያይ ህግ አጥር ስር ነው፡፡ ይህንንም ህግ የሚያስከብረው እራሱን የቻለ ነፃ የመንግስት አካል ይሆናል፡

እንግዲህ በፖለቲካ ሊበራሊዝም ስር የሚጠቃለሉት እነኝህ ሀሳቦች በአብዛኛው ከላይ ዘውግ ተኮር በሆነ መልክ የተደራጁትም ሆነ ዘውግ ዘለል በሆነ መልክ የተደራጁት በኢትዮጵያ ያሉ የፖለቲካ ሀይሎች ሁሉም እንፈልገዋለን የሚሉትን መብቶች ያካተተ የፖለቲካ ስርአት ነው ማለት ነው የሚፈጥረው፡፡ ስለዚህ ይህ በራሱ በሚፈጠረው ስርአት ላይ ሰፊ አገራዊ ስምምነትን የያዘ ስለሚሆን ለዚያ ስርአት መተከል የሚደረግ ትግል ጠንካራ የሆነ የአስተሳሰብ መሰረት ያለው ነው የሚሆነው፡፡

ከዚያ በተጨማሪም ግን ይህን አመለካከት ከዚህ በፊት ፖለቲካችንን ከተጠናወቱት አመለካከቶች ጋር ሲመዘን (ለምሳሌ የግራው አመለካከት) ቀኖናዊ አይደለም፡፡ የሚሰራውን እያየ በሀቅ ላይ በመመስረት በብልህነት የሚነቃነቅ ነው፡፡ ለድርድር፤ ለሰጥቶ መቀበል እራሱን ክፍት ያደረገ፤ ለሁሉም ችግር አንድ ወጥ የሆነ መልስ አለ ብሎ የማያምን ለዘብተኛ አመለካከት ነው፡፡ ከዚያም

በላይ ግን አዲሱ አመለካከት የሚጠይቀው የአመለካከት ትክክለኛነትን ብቻ ሳይሆን አዛኝ ስሜትን፤ ለተጠቁና ለተበደሉ መቆምንም፤ ጠንካራ የሆነ በዜጎች መሀከል የሚበለፅግ የአብሮነት ስሜት (solidarity to fellow citizens) ነው:: ለዚህ ነው ይህንን አመለካከት እንጋራለን የሚሉ ሀይሎች በሙሉ፤ እምነታቸው ከምር ከሆነ አብረው ለመታገልና ይህንን ስርአት እውን ለማድረግ ሊያቅታቸው አይገባም የምለው::

## 5) ይህን ለማምጣት በተግባር ማድረግ ያሉብን እርምጃዎች

በአመለካከትና በእምነት ደረጃ ያሉት ልዩነቶች እንደዚህ ጠባብ ከሆኑና ትግሉን ማስተባበር እንደሚገባ ከላይ ባቀረብኩት መከራከሪያ ላይ መጠነኛም ቢሆን ስምምነት ካለን ንግግሩ ዝም ብሎ የወሬ ብቻ እንዳይሆን በተግባር ደረጃ በፖለቲካ ሀይሎች እንዲሁም በዜጎች መደረግ አለባቸው ብዬ የማስባቸውን አንዳንድ እርምጃዎች ለውይይት መክፈቻ እንዲሆን ላነሳሳና ይህን አጉል የረዘመ ንግግር ልቁዋጨው::

ሀ) በመጀመሪያ በመሀላችን ያለውን ጥልቅ የመጠራጠር ስሜት በጋራ ትግል መቀነስ፤ ቀስ በቀስም ማጥፋት ያስፈልጋል:: ይህን ደግሞ በፖለቲካ ሀይሎች መሀከል ብቻ ሳይሆን በፖለቲካ ድርጅት ደጋፊዎች አልፎም በመላው ህብረተሰብ ውስጥ ዘልቆ እንዲገባ ያስፈልጋል:: ለዚህ የመጀመሪያው እርምጃ ሁላችንም በግለሰብ ደረጃ የተተከለብንን ሌላውን የመጠራጠር፤ የመናቅ ወይንም የመጥላት ጂኒ በግላችን አውልቀን ለመጣል መንቀሳቀስ አለብን::

ለ) ምንም ዘውግ ሳንቆጥር፤ በየትኛውም የሀገራችን ክፍል ለሚደረግ ግፍና አፈና፤ የሰብአዊ መብት መጣስ በጋራ መቆምና መታገል አለብን:: በአሁኑ ጊዜ በኦጋዴን አካባቢ በዜጎቻችን ላይ የሚደረገውን አይን ያወጣ አረመኔያዊ ጭፍጨፋ፤ በኦሮሚያ ክልል የሚደረገውን ማቆሚያ የሌለው ወከባ በአንድ ድምፅ በተግባር መቃወም አለብን::

ሐ) በምክንያት ላይ የተመሰረተ፤ ጠንካራ የማወቅ ፍላጎትና ክፍት አእምሮን የሰነቀ፤ በምንም ሁኔታ ህይወታችን የተሳሰረች መሆኑን ያመነ የልብ ውይይት ከሚመስሉን ጋር ብቻ ሳይሆን የተለዩ ይመስሉን ከነበሩ ወገኖቻችን ጋር ማድረግ፤ በዚህ ዙሪያ ምሁሮቻችንና የሲቪክ ማህበረሰቡ አባላት ይህንን ውይይት በአስቸኩዋይ የሚጀምሩበትን መንገድ ማመቻቸት ይገባናል::

መ) ይህን ውይይት በማህበረሰቡ አባሎች መሀከል ሲደረግ በቀጣይነትና በተያያዘም በፖለቲካ ሀይሎች መሀከል በመርህ ላይ የተመሰረተ፤ወደ ተግባር የሚወስድ አጣዳፊ ውይይት በማድረግ የዴሞክራሲ ትግሉ በአንድ አቅጣጫና በአንድ አመራር የሚጉዋዝበትን መንገድ በአስቸኩዋይ መቀየስ ይገባናል።

ሰ) የፖለቲካ ሀይሎች እንዲህ አይነቱን ጥምረት በሚፈጥሩበት ጊዜም በሌሎች የሲቪክ ማህበር ድርጅቶች መሀከልም ተመሳሳይና ቀጣይነት ያለው ውይይት በማድረግ በነሱም በኩል ትግላቸውን ማስተባበር ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ሀይሎች ያለበቂ ምክንያት (ከዴሞክራሲና ከእኩልነት ጋር ባልተያያዘ) ትግሉን በማስተባበር በኩል እክል ቢፈጥሩ እነሱን ለመገሰፅና በመስመር ለማስገባት የሚያስችል ነፃነትና ጉልበት እንዲያበለፅጉ መርዳት ይገባናል።

ረ) በባህል ረገድ ሆን ተብሎ የሚዘጋጁ የባህል ትርኢቶችና ፕሮግራሞች ለሁሉም የማህበረሰቡ አባላት በሚሆን መልኩ እያዘጋጁ ሁሉም ኢትዮጵያውያን በጋራ እንዲቁዋደሱት ብቻ ሳይሆን አንዳችን ስለሌላኛችን ባህል የምናውቅበትን ሁኔታ በሰፊው ማዘጋጀት። ይህም ሁሉም የራሱን ባህል ለማበልፀግ የሚያደርገውን ጥረት በሚያግዝ መልኩ የሚዘጋጅበትን መንገድ ማስላትና ማስፈፀም። ለዚህ እንቅስቃሴ በተለይ በባህል መስክ የተሰማሩ ከሁሉም ዘውጌ ማህበረሰባት የተውጣጡ ዜጎቻችን ቅድሚያውን ወስደው እንደሚንቀሳቀሱ እምነቴ ነው።

እነኝህን እርምጃዎች መውሰድ በምንም አይነት ሊያቀተን አይገባም። በደላችንና ውርደታችን የማናችንም ጫንቃ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ሆኖአል። ትግሉን አስተባብሮ በደልን ለመጋፈጥ የሚያስፈልገን የጋራ አላማ አለን። የምንደርስበትን እናውቃለን እናምንበታለንም ማለት ነው። መለስ በረከትና ስብሀት እንደሚያስቡትና እንደሚመኙት ለመተባበር የሚያስችል ብልህነቱ ይጠፋናል ብዬ አላምንም። መቼም የሚገዙን በእውቀት በልጠውን ነው ብሎ የሚያስብ ያለ አይመስለኝም። እስኪ ለአንድ ደቂቃ ቆም ብላችሁ አስቡት። እንዲህ አይነት ትብብር ቢፈጠርና ትግሉን ቢያስተባብር እነመለስ ምን ያህል ጊዜ በስልጣን ይቆያሉ ብላችሁ ታስባላችሁ? የኢትዮጵያ ወታደር እነመለስን በስልጣን ለማቆየት ምን ያህል ህይወቱን ይሰጣል ብላችሁ ትገምታላችሁ? እነሱ በስልጣን እስከአሁንም የቆዩት ባላቸው ጥንካሬ ሳይሆን በእኛ የውስጥ ድክመት ነው። በኛ መተባበር አለመቻል ነው። በሉ ወሬ አቁመን ወደ ስራ እንግባ።

**በትዕግስት ስላዳመጣችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ**